# “ ከማመልከት አንቦዝንም ”

## ምርጫ 2002ን አስመልክቶ ከአንድ ኢትዮጵያ ድርጅት የተሰጠ መግለጫ

የአራተኛው ጊዜ አገራዊ ምርጫ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ቢኖረውም በአሁኑ ጊዜ በስፋት በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ አነጋጋሪ ሆኗል:: ድርጅታችን አንድ ኢትዮጵያ ላለፉት 21 ዓመታት በአገራችን በኢትዮጵያ ውስጥ አንድነት ፣ሠላም ዲሞክራሲ ይኑር ይመጣል እያለ የሚታገል ድርጅት እንደሆነ ከኛ ጋር ለ21 ዓመታት የቆያችሁ ሁሉ የምታስታውሱት ነው:: ታዲያ ኢህአዲግን አጀማመሩን በጣም ኮንነን የአገራችንን አንድነት ያጠፋል ብለን ፈርጀን ነበር:: ከ1998 ዓ.ም በኂላ ግን አገራችን ላይ የሻዕቢያን ጥቃት እመክታለሁ ባለ ጊዜ አብረን ተጉዘናል ደግፈናልም:: በሱማሌ በኩል ለመጣብን ጥቃትም እንደዚሁ ከመንግስት ጎን ቆመናል:: በ1997 ዓ.ም ደግሞ የዲሞክራሲው ስርዓት በር ተከፍቷል፣መድበለ ፓርቲ እንዲመጣ አድርጓል ብለንም ደግፈናል ብዙም ተቃዋሚዎች ምክር ቤት እንዲገቡ ሆኗል:: ለዚህ 2002 ዓመት ምርጫም የነበረን ግምት ኢህአዲግ በስፋት ያሸንፋል በማለት ተንብየንም ነበር:: ነገር ግን በፍፁም የተገኘውን ውጤት አልጠበቅንም ነበር::

ኢህአዲግ በርግጥ አሸንፏል ግን በዚህ አይነት ውጤት ማሸነፍ አንድም ተቃዋሚው ድርጅት እንዳልነበረ (በጣም ደካማ ነበር) አልያም ኢህዲግ በጣም ጠንካራ ነው:: የሚለውን ሐሳብ መስጠት ይቻል ይሆናል:: ነገር ግን አንድ ሃቅ አለ የመወዳደሪያ መስኩ ለሁሉም እኩል ነበር የሚለው አጠያያቂ ብቻ ሳይሆን የውጤቱ ዋና ምክንያት ነው ብለን እናምናለን ::

204 የክስ አቤቱታዎችን ይዞ የተጠናቀቀው የዘንድሮ የ2002 የምርጫ ዘመቻ ከሁለት ሰዎች ህይወት ማለፍ በስተቀር በሌላ መልኩ ፍፁም ሰላማዊና በተዘጋጀለት የጊዜ ሰሌዳ እንደ ተጠናቀቀ በሁሉም ታዛቢዎች ዘንድ ተመስክሯል:: ከ63ቱ የፖለቲካ ተወዳዳሪዎች ውስጥ አላማቸውን በቴሌቭንና በሬድዮን ለህዝብ ለማስተላለፍ እድል ያገኙት 5 የፓለቲካ ድርጅቶች ብቻ ሲሆን የተቀሩት 58ቱ ተወዳዳሪዎች ግን መራጩን ህዝብ በፖስተርና በበራሪ ወረቀቶች ለማግኘት ጥረት ሲያደርጉ ተስተውለዋል:: በቴሌቭዥንና በሬድዮን በተደረጉት 9 ክርክሮች ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ችግር አንስቶ እስከ ውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ባሉት ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ 5ቱም ድርጅቶች ሞቅ ያለ ውይይት አድርገዋል:: «እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ» ተባብለዋል::

በክርክሩ ውስጥ አቶ ልደቱ አያሌው ከተቃዋሚዎች አቶ ሬድ ዋን መሀመድ ደግሞ ከኢህአዲግ የህዝብን ቀልብ የሚስብ የቃላት ጦርነት ተለዋውጠዋል፡፡ ጊዜው ደርሶ ምርጫው ሲካሄድ ከተመዘገበው 32 ሚሊዮን ህዝብ 29 ሚሊዮን ህዝብ ድምፁን ሰጥቷል፡፡ በቆጠራው ውጤትም ለመጀመሪያ ጊዜ የህዝቡ የምርጫ ፍላጎት ከፍ ባለበት በዚህ ወቅት የገዢው ፓርቲ አብዛኛውን መቀመጫ ጠራርጎ ወስዶል፡፡ የተገኘው ውጤት አስገራሚ ብቻ ሳይሆን አስደንጋጭም ነው ተብሏል፡፡ ውጤቱ ተቃዋሚዎች ብቻ ሳይሆን ኢህአዲግንም ጭምር አስገርሟል፡፡

አሸናፊው ኢህአዲግን ሳይቀር እንደዚህ ሊያስገርም ያስቻለው የምርጫው ውጤት ምን ቢሰራ ነው እንዴትስ ቢከናወን የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ ጥያቄው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩትም በዋናነት የሚጠቀሰው ግን የገዢው ፓርቲ ኢህአዲግ የምርጫ 97 የቅንጅትን አይነት የቅስቀሳ ስልት መከተሉ እንደሆነ የአንድ ኢትዮጵያ ድርጅት ያምናል፡፡ ኢህአድግ ልክ እንደ ቅንጅት ከተራ ለፍቶ አዳሪዎች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ባለሀብቶቸ ያሉትን ነጋዴዎች በሙሉ ከጎኑ ለማሰለፍ ችሏል፡፡

ቅንጅትና ኢህአዲግን ምን አንድ አደረጋቸው ትሉ ይሆናል? ቅንጅትና ኢህአዲግን አንድ ያደረጋቸው አላማቸው ሳይሆን የተከተሉት የፓለቲካ ቅስቀሳ ተመሳሳይ በመሆኑ ነው፡፡ቅንጅት በምርጫ 97 ህዝቡን ከዳር እስከዳር ከጎኑ እንዳሰለፈው ሁሉ ኢህአዲግም ዘንድሮ ህዝቡን ከጎኑ ሊያሰልፍ ችሏል፡፡ በምርጫ 97 ቅንጅት የተጠቀመበት የፖለቲካ ስልት ፤ ላይ ላዩን ሰላማዊ ይምሰል እንጂ ውስጥ ውስጡን ግን ጥላቻ ነበር፡፡ ቅንጀት ያራመደው የጥላቻ ፖለቲካ ነበር፡፡ ጥላቻው መስመሩን ለቆ «ዕቃ ወደ ቀበሌ ትግሬ ወደ መቀሌ» እስከ መባል ተደርሶ ነበር፡፡ ገጀራ፣ ቆንጨራ፣ ሰንጢ ወዘተ የመሳሰሉት ስለታም መሣሪያዎች በሙሉ ለዚህ እኩይ ተግባር ማስፈፀሚያ ከገበያ ላይ ተሸጠው አልቀው ነበር፡፡ ቅንጅት በጥላቻ ቀስቀሳ በአዲስ አበባና እንዲዚሁም በተቀሩት የሃገሪቱ ዋናዋና ከተሞች ውስጥ ኢህአዲግን 3 ለ 1 ወይንም ከዚያ በለይ በሆነ ውጤት ሊያሸንፍ ችሏል፡፡ ህዝቡም ቅንጅትን ወዶ ሳይሆን ኢህአዲግን ጠልቶ ድምፁን ለቅንጅት እንደ ሰጠ ያለፈው አምስት ዓመት የምርጫ ትውስታችን ነው፡፡

ጥላቻ በምርጫ 97 በሃገሪቱ ምድር ላይ እንደ ሰደድ እሳት እንደ ተቀጣጠለው ሁሉ በዘንድሮ ምርጫ ደግሞ የፍራቻ ጥላ አጥልቶ ፍራቻ በኢትዮጵያ ነግሶ ነበር፡፡ ቅንጅት በምርጫ 97 ጥላቻን እንደ መሳሪያ እንደተጠቀመበት ሁሉ ገዢው ፓርቲ ኢህአዲግ ደግሞ ዘንድሮ ፍራቻን ተጠቅሟል፡፡ ፍራቻን በህዝቡ ስነልቦና ውስጥ በተዘዋዋሪ መልኩ በመጨመር የምርጫው ውጤት ወደ እራሱ ፓርቲ እንዲያዘነብል አድርጓል፡፡ የትምህርት እድል፣የሥራ እድል፣ የኑሮ ዋስትና ወይንም ተቀዳሚ ዜጋ ሆኖ ለመገኘት የግድ

የኢህአዲግ አባልነት በሚጠየቅበት ጊዜ ነው ብሎ ያመነ ህዝብ የተገኘው ከፍተኛ ውጤት እምብዛም ሊያስገርም አይችልም:: ከጅምሩ አምስት ሚሊዮን ህዝብ አስመዝግቦ በተጨማሪ ደግሞ አንድ አባል 5 አባሎችን መመልመል አለበት በተባለበት በዚህ የወከባ ፖለቲካና ጫና ውስጥ ኢህአዲግ አሸነፈ ቢባል ሊገርመን አይገባም:: በዚህ አይነት የአባል ምልመላና የፓለቲካ ሥራ ኢህአዲግን ከቻይና የኮሚኒስት ፓርቲ በስተቀር የሚስተካከለው ሃይል ማግኘት አይቻልም::

በምርጫ 97 ጥላቻ እንደነገሰው በዘንድሮ ደግሞ ፍራቻ ነግሶ ነበር:: ፍራቻ በህዝቡ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በገዢው ፓርቲ በኢህአዲግ ውስጥም ነበር:: ኢህአዲግ ለሁለተኛ ጊዜ የምርጫ 97 አይነት ሽንፈት ይገጥመኛል ብሎ በከፍተኛ ፍራቻ ውስጥ ነበር:: በፍራቻ ስሜት የተንቀሳቀሰው ኢህአዲግ ከሚጠብቀው በላይ ከፍተኛ ድምፅ አግኝቷል::

በቀጥታ የቴሌቭዥን የፓለቲካ ክርክሮች እንዳይተላለፉ ፣ ለተቃዋሚዎች በቂ የአየር ሰዓት አለመስጠት ወዘተ ለኢህአዲግ ፍራቻ ዓይነተኛ ምልክቶች ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ:: ነጋ ጠባ የመንግስት መገናኛ ብዙኃን "ምርጫው ሠላማዊ እንዲሆን" ምርጫው ሠላማዊ እንዲሆን ሠላማዊ እንዲሆን እያሉ የሚያስተላልፉትን መልዕክት ህዝቡ በተቃራኒው በመውሰድ የምርጫው እለት አንድ ነገር ሊፈጠር ይችላል በማለት በፍርሀት ተሸብቦ ነበር::

ሌላው እንኳን ቀርቶ አንድ ሰው የተለያዩ መስሪያ ቤቶች ጉዳይ ለማስፈፀም ሲሄድ የሚያገኘው መልስ ከምርጫው በኋላ ተብሎ ነበር:: ሌሎች ደግሞ የስልክ መስመሮች እንኳን ሳይቀሩ በሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ቋንቋ ተጠልፈው መንግስት እያዳመጣቸው ነበር ብለው ይፈሩ ነበር::

ህዝቡ ከራሱ ፍራቻ ለመውጣት "ምን አለ ይሄ ምርጫ ቶሎ ደርሶ በተገላገልን" እስከ ማለት ድረስ ፈርቶ ነበር:: ህዝቡ በራሱ የፈጠረው ፍራቻ እና መንግስት የፈጠረው ፍራቻ በአንድ ላይ ተጣምረው የዘንድሮን ያልተጠበቀውን የምርጫ ውጤት ለማስገኘት ችለዋል::

ቅንጅት ፓርላማ አንገባም ብሎ የዲሞክራሲ ሂደቱን ወደ ኋላ እንደጎተተውና ዛሬ ከተወቃሽነት እንዳልዳነው ሁሉ ዘንድሮም ለተገኘው አሳዛኝ የምርጫ ውጤት ምንግዜም ገዢው ፓርቲ ከተወቃሽነት ሊድን የሚችል አይመስለንም::

ዘንድሮ ተቃዋሚዎች 2 መቀመጫ ወንበር ብቻ ማግኘታቸው ውጤቱ ከምርጫ 97 ጋር የተያያዛ የራሱ የሆነ አባዜ እንዳለው ቢታወቅም ፤ የአውሮፓ የምርጫ ታዛቢዎች ግን ውጤቱን ከስፖርት መኪና ጋር አነፃፅረውታል:: የስፖርት መኪና ከሁለት ሰው በላይ ማሳፈር እንደማይችለው ሁሉ የኢትዮጲያ ፓርላማም እንደዚሁ ከሁለት ሠዎች በላይ

መያዝ ባለመቻሉ የተሰነዘረ ትችት ነው:: የኢትዮጵያ ምክር ቤት የስፖርት መኪና ተብሏል::

75 ሚሊዮን ህዝብና ከ 80 በላይ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች የሚነገርባት አገራችን ከሁለት ተቃዋሚዎች በላይ በአሁኑ ጊዜ ማስተናገድ አለመቻሏ አሳዛኝ ብቻ ሳይሆን እንደተባለው አስደንጋጭም ነው:: ያውም አንደኛው ተቃዋሚ ዶ/ር አሸብር ከኢህአዲግ በላይ እህአዲግ ናቸው ተብሎ በሚታመንበትና እራሳቸው ግለሰቡ ሳይቀሩ በሚያምኑበት ሁኔታ እንዴት ተደርጎ ነው ተቃዋሚዎች 2 መቀመጫ አገኙ ተብሎ የሚነገረው:: መነገር የነበረበት ተቃዋሚዎች 1 መቀመጫ ብቻ አገኙ ተብሎ ነበር::

የተከበራችሁ የአንድ ኢትዮጵያ ሬድዮን አድማጮች በዘንድሮ ምርጫ ተቃዋሚ ሃይሎች ሳይሆኑ የተሸነፉት የዲሞክራሲ ስረአቱ ነው:: ከምርጫ ምክር ቤት የተባረሩት ተቃዋሚ ድርጅቶች ሳይሆኑ ፤ ከምክር ቤቱ የተባረረው የዲሞክራሲው ስረአቱና የዲሞክራሲው ባህሉ ነው::

የዛሬቱ ኢትዮጵያ ማንን ትመስላለች ቢባል መልሱ የዘንድሮው የምርጫ ውጤትን ትመስላለች ነው:: አገራችን: የተቃዋሚ ሃይሎችና የኢህአዲግ የፖለቲካ ድምር ውጤት ናት:: ተቃዋሚ ሃይሎች ከኢህአዲግ ጋር ተደምረው የዛሬቱን የሀገራችንን የፖለቲካ ባህል ፈጥረዋል:: ሊፈጥሩም ችለዋል::

እዚህ ላይ የዲያስፖራው የፖለቲካ አመለካከትም በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ዛሬ ላለንበት የፖለቲካ ባህል የራሱ የሆነ ድርሻ አበርክቷል:: ዲያስፖራው እንደ ምርጫ 97 ዘንድሮ የሚደግፈው አንድም ሀይል አላገኝም:: ነገር ግን ያገኘው አንድ ትልቅ ድል አለው:: ድሉ ተቃዋሚዎች በሙሉ መሸነፋቸው ነው:: ዲያስፓራው ልክ እንደ ኢህአዲግ በምርጫው ውጤት እጅግ ተደስቷል:: ዲያስፓራው ከኢህአዲግ ጋር አብሮ መስራት አይቻልም ለሚለው የዘመናት አባባሉ የዘንድሮ ምርጫ ውጤት አይነተኛ ማስረጃ ሊሆንለት ይችላል:: በዚህም ሊንቀሳቀስ ይችላል::

ዲያስፖራው የቀድሞ ተቃዋሚ የፓርላማ አባሎችን እንደተቃዋሚ ሀይሎች መቼም ቆጥሮቸው አያውቅም:: እንደነ ፐ/ር በየነ ጴጥሮስ ዶ/ር መራራ ጉዲና ወዘተ ያሉትን በሙሉ ኢህአዲግን ዲሞክራቲክ ለማስመሰል የሚታገሉ ግለሰቦች እንጂ የሠላማዊ ታጋዮች አድርጎ ወስዶአቸው አያውቅም :: አንዳንዴም ኢትዮጵያዊነታቸውን ሳይቀር እጥያቄ ውስጥ እያስገባ ሲያዋርዳቸውና ሲሰድባቸው እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው:: እነዚህ የሰላማዊ ታጋዮች ኢህአዲግን በታገሉበት ሃይላቸው በተመሳሳይ መልኩ

እንደዚሁ የዲያስፖራውን ፅንፈኞች ሲታገሉ ኖረዋል። ፐ/ር በየነ ጴጥሮስ ዶ/ር መራራ ጉዴና አቶ ቡልቻ ደመቅሳ አቶ ተመስግን ዘውዴና አቶ ልደቱ አያሌው ወዘተ ከምክር ቤት መውጣት ለኢህአዲግ ድል እንደሆነው ሁሉ ለዲያስፖራውም እንደዚሁ የጋራ ድል ሆኖ ሊያስደስታቸው ይችላል።

የተከበራችሁ ታዳሚዎቻችን

የአንድ ኢትዮጵያ ድርጅት ምርጫ 97ን አስመልክቶ ፓርላማ አትግቡ የሚለውን የዲያስፖራና የቅንጅትን ፀረ ዳሞክራሲ አቋምን እንደተቃወመው ሁሉ የዘንድሮ የኢህአዲግን የምርጫ ውጤትንም እንደዚሁ በተመሳሳይ መልኩ ኢህአዲግ ማሸነፉን ሣይሆን ተቃዋሚዎቹን ያገለለ ምክር ቤት ስለሆነ ይቃወመዋል።

የአንድ ኢትዮጵያ ድርጅት ይሄን ብልጭ ድርግም እያለ የሚጓዘውን የሀገራችን ዲሞክራሲን ከናአካቴው እልም ብሎ እንዳይጠፋ የሚያደርግ አዲስ ተስፋ አለው። መጪውን 5 ዓመት በናፍቆት እንድንጠባበቅ የሚያደርገን አዲስ ተስፋ ነው። ተስፋው በተቃዋሚና በኢህአዲግ መሪዎች ትከሻ ላይ የወደቀ ትልቅ ተስፋ ነው። ተስፋው የተቃዋሚና የኢህአዲግ መሪዎችን ለመጪው 5 ዓመት በፍቃደኝነት እራሳቸውን አግልለው በአዲሶች ሲተኩ ማየት ነው። ተስፋው የ1960ዎቹ የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች የጥላቻ ፖለቲካ በዚሁ በዘንድሮ ምርጫ አክትሞ ቀጣዩ 5 ዓመት ከጥላቻ፡ ከቂም በቀልና ከአወኩሽ ናቁሽ የፀዳ ፣ አዳዲስ ፖለቲከኞችን የምናይበት ልዩ ተስፋ ነው። ተስፋው በምክር ቤት ውስጥ አዳዲስ ተመራጮችን ማየት ነው። ተስፋው የኢትዮጵያ ተስፋ ነው። ተስፋው ተስፋ ብቻ ሳይሆን ራዕይም ጭምር ነው። ተስፋው ለቀጣዩ 5 አመት ካሁን እንድንሰራ የሚያበረታታ አዲስ ተስፋ ነው።

ስላዳመጣችሁን እናመሰግናለን።

በዘንድሮ ምርጫ የተሸነፉት ተቃዋሚ ኃይሎች ሳይሆኑ ፤ የተሸነፈው እያደገ የመጣው የዲሞክራሲ ስርአታችን ነው። ከአዲስ አበባ ምክር ቤት የወጡት የተቃዋሚ ድርጅቶች ሳይሆኑ ፤ ከምክር ቤት የወጣው የተቃዋሚዎች ክርክር ነው። ከምክር ቤት የወጣው የነ አቶ ተመስገን ዘውዴ ክርክር ነው። ከምክር ቤት የወጣው የነ አቶ ልደቱ አያሌው ክርክር ነው። ከዚህ በላይ ያደመጣቹሁት ምርጫ 2002ን አስመልክቶ ከአንድ ኢትዮጵያ ድርጅት የተሠጠውን መግለጫ ነው።